# ቀስተ ደመናዊ ቅንጅት

## ከይልቃል አንድነት (ዲሲ)

ሲባል ሰምቼ ነው እንጅ ይኸን ስም እኔ አላወጣሁም። ላወጣውም አልችልም። መጠየ
ቅ ያለባቸው ለዚህ ስም የሚሯሯጡት ናቸው። እንቁጭ በሉ።

እኔ እንኳ አሽሟጣጭ አይደለሁም። አሁን ግን በድፍረት ሟሽሟጠጥ አለብኝ። የማይ
ታለፍ ሽሙጥ አይታለፍም። የአሽሟጣጭ ሰው አፉ ጠማማ ነው ቢባልም የእኔ አፍ ሞ
ጥሟጣ ነው እንጅ ጠማማ አይደለም። ለነገሩማ ሁሉም ሞጥሟጣ ሲሆን እኔ ምን ላድር
ግ።

ምንም ይሁን ምንም ስለቀስተደመናዊ ቅንጅት ያለውን ሽሙጥ ቀስ ብላችሁ፣ ዐይናችሁን
ከፍታችሁ፣ አእምሮአችሁን አስፍታችሁ አንብቡ። ከዚያ በሁዋላ ከፈለጋችሁ በእኔም ላ
ይ ልትሞጣሞጡ ትችላላችሁ። ሽሙጡን በጥንቃቄ መመልከቱ ቢያንስ ቢያንስ የአሽሟጣ
ጩን ያህል ግንዛቤን ለማግኘት ያስችላል።

ለመሆኑ ቀስተደመናዊ ቅንጅት ማለት ምን ማለት ነው የምትሉኝ ካላችሁ፤ ቅንጅትን መ
ስሎ ቀስተደመናን አህሎ፣ ዲያስፖራውን የሚያተራምስ የአራዳ ልጆች የድጋፍ ማሰባሰቢ
ያ መድረክ ማለት ነው። የዘለቄታ አላማውም የተቀናጁትን ወዳጆቹን በመናቅና መብለጥ
ለጥ (outsmart) በማድረግ በቅንጅት ስም መንግስት ለመያዝ መሯሯጥ ነው ይባላል።
አይገርማችሁም። ጉድ እኮ ነው።

በቅንጅት ስም የተሰባሰቡት ሁሉ እንታገላለን ይሉናል። ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም፣ ዴሞ
ክራሲና ነጻነት እንታገላለን ይላሉ። በአሁኑ ጊዜ ከማን ጋር እየታገሉ እንደሆነ ግልጽ ነ
ውን? መቸም ይኸ አዚማም ወያኔ ከንስሀ አባቱ ከአባ ዲያብሎስ ያገኘው መተት ሰምሮለ
ት ይሆን የሚታገለው የደከመለት? የሚሉ አልጠፉም። እኔ ደግሞ የእኛ ነገር ከሞኝ ደጃ
ፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ እየሆነብኝ እደመማለሁ። «ሲነድ ሲቃጠል የሚጨስ እሳት
ነው» የሚለው የአይዋ ገሞራው (ሃይሉ) አባባል እየታወሰኝ።

ያማ ባይሆን ኖሮ በ1997 ኢ. ም. ምርጫ እጢው ዱብ ብሎበት፣ ይይዘው ይጨብጠውን
አጥቶ፣ እራሱ ባወጣው የጨዋታ ህግ ተሸንፎ ሲያፍር ታይቶ አልነበረምን። ያስ የሆነው
ህዝቡ ከቅንጅት ጋር አንድ ሆኖ መስዋእትነት ስለከፈለ አልነበረምን? ይህንን ማን ያስተባ
ብላል? የሚሉ ብዙዎች ናቸው። እኔ ደግሞ ትግሉም ድሉም የጋራ ነው እላለሁ - የብ
ዙዎች መስዋእትነት፣ የአመታት ድምር ውጤት- ምንም እንኳ የተዋጣልኝ ነጋዴ ባልሆን
ም።

ታዲያ ቅንጅትን ምነው ነፋስ ገባበት? ያንጊዜ የነበረው ድንጋጤያቸው ተገፍፎላቸው፤ አ
ሁን እነዋልታ፣ አይጋ ፎረም፣ ሪፖርተር ወዘተ የቅንጅትን መሪዎች በራሳቸው ምላስ ሲነ
ድፏቸው የሚታየው ለምንድር ነው? አንባቢና ሰሚ ያልነበረው የመገናኛ ብዙሃን የእለት
እራት እንዴት ሊሆኑ ቻሉ? «ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ» እንደሚባለው ሌላውን ትግልና ውድ
ድር አቁመው የመግለጫ ውድድር ሲያካሂዱ፣ ለዚያውም አንዱ ያለው ከሌላው ጋራ የማ
ይገናኝ እየሆነ ለምን ገመናቸውን ይገልጣሉ? እያሉ የሚቆረቆሩ ብዙ ናቸው። እነልዴቱ
አያሌውማ እንዲያውም የቅንጅትን ህልውና መክዳት ብቻ ሳይሆን አልፈውም ያሾፉሉ።
አያሳዝንም?! ሲያዝኑ ታዲያ «ከሞኝ በራፍ ሞፈር ይቆረጣል» የሚለውን አባባል ተመግበ
ው በ«ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው» ሌላ አባባል ያወራርዱት። የእናንተን አላው
ቅም እንጅ እኔስ እርር ድብን ብያለሁ።

ወደ ጀመርኩት ልመለስ። መቸም ራሳቸው በሚናገሩት እንደተገለጠልኝ ሽሙጥ ሳይሆን
ሀቁን ልንገራችሁ። ቀስተደመና ከተቀናጀ በሁዋላ የውሃና የዘይት ውህደት ይዞ የቆየ ይ
መስለኛል። ይኸም ስም ማጥፋት ሳይሆን ለአሽሟጣጩ አባባሌ ዋቢ የሚቆጠሩ ብዙ ማ
ስረጃዎች አሉ። በቅድሚያ የታላቁ ሊቅ ፕሮፌሰር መስፍን የኑዛዜ ምስክርነት መሬት የ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሚወድቅ አይደለም። አሁን ገሃድ እየወጣ ነዋ! የዶክተር ብርሃኑና የኢንጅነር ሃይሉን ት
ክለ ሰውነት ከሚያጣጥሉ ጭፍን ደጋፊዎችም ቢሆን አፈትልኮ የሚወጣ ሀቅ አለ። የቅን
ጅት መሪዎች ወደየአቅጣጫው ከተጓዙ በሁዋላ የውስጥ መቋሰላቸውንና አንዱ በሌላው ላ
ይ የሚያደርገውን መብለጥለጥ፣ አመላቸውንና ገመናቸውን ወሬ የራባቸው ሬዲዮኖች፣ ጋ
ዜጦች፣ ድረ-ገጾች፣ የእንካ ስላንቲያ ፓልቶኮች ቁርስ፣ ምሳና ራት ሲያደርጉት መቆየታቸ
ውን ጆሮ ላለውና ጣቱ መጅ እስኪያወጣ ድረ-ገጽና ሬዲዮ ለሚጎረጉረው ሁሉ ምስጢር ነ
ው አይባልም። ከራሳቸው በቀር ሌላ የሚለውን ከማይሰሙት በቀር ህዝቡ ብዙ ነገር ሲ
ታዘብ ቆይቷል። እንደየቡድኑም የየራሱ ትርጉምና አራጋቢ በብዛት ተፈጥሯል። ይኽ እ
ኮ ሽሙጥ አይደለም።

መቸም ጠብና አለመግባባት እንዳለ ታውቋል። ለምን ተጣሉ? ዋናው ምክንያት አለመተ
ማመን ነው። ዋናው ምክንያት፡-

ብልጥ ለብልጥ!
አይን ፍጥጥ!

እንደሚባለው ነው። በአሽሟጣጮች አመለካከት፣ ልብ ለልብ እንዳይገናኙ ያደረጋቸው
ቅንጅት ከተመሰረተ በሁዋላ የታየው መሽዋወድ ነው። የአራዳ ልጆች የመርካቶ ቁጭ በ
ሉ። በቤተመንግስት ደግሞ በደርጉ ዘመን-አገዛዝ እንደተሞከረው ሁሉ «ወዛዊ ሰደድን»
ለመፍጠር ውስጥ ውስጡን የተጧጧፈው ምልመላ ምስጢሩ ተደረሰበት። መተፋፈር ብ
ቻ ሳይሆን መማረርም መጣና የተመነደጉት የሚጠቅሙ ሰዎች በቀላሉ ተቀጩ። ኢንጅነ
ር ሃይሉም ቦታውና ጊዜው አላመቻቸው ብሎ ነው እንጅ የተሰማቸው የዚያው አይነት ነገ
ር እንደሆነ ከአፋቸው በሚወጣው ትኩሳት ይታወቃል። አለመተማመን ክፉ ነው። በግ
ልጥ እንደሚታየው እነዶክተር ብርሃኑም ሲያደርጉ የቆዩት መሰል ድርጊት ነው የሚሉ ግ
ልጽ ማስረጃ አላቸው። ቅንጅት ሲቋቋም ከመቶ ዘጠና ቁልፍ ቦታዎችን በምሁራዊ ትክለ
ሰውነት በመያዝ፣ በምላጭነት ሊፎካከራቸው የሚችለውንና የነዶክተር ብርሃኑን ተንኮል የ
ሚያውቀውን፣ከብዙ አባላትም ጋር የመጣውን ልደቱ አያሌውን እንደዋንጫ ቂጥ አውልቀ
ው ጣሉት። ዝርዝሩን ከእኔ የበለጠ ታውቁታላችሁ።

ከዚያም ዋናውን ቅንጅት ሳይሆን ቀስተደመናዊ ቅንጅትን ተመሳስለው መምራት ጀመሩ።
ለኢንጅነር ሃይሉና ለሌሎች ሁለት የመኢአድ አባላት ብቻ ቦታ ሰጥተው የድምጽ ብልጫ
በሌለው ቅምጥ ሊቀመንበር አማካይነት የፈለጉትን ሲሰሩ ቆዩ። ጉዳዩ ከጊዜ በሁዋላ ሲከ
ሰትላቸው ኢንጅነሩ በየመድረኩ በገመምተኛ ቃላቸው የሆነ ያልሆነውን ሲደሰኩሩ ከቆዩ
በሁዋላ በተለይ በዲያስፖራ የተሰራው ሴራ ተጨማሪ ጤና ስለነሳቸው አዲስ አበባ ያላቸ
ውን ሰው አሰባስበው በክብር ከቢሮአቸው ሆነው ሊያወጡ የሚገባቸውን የማገጃ ውሳኔ አ
ስተላልፈው በሰለጠኑት የሬዲዮ ጋዜጠኞች በአዲሱ አበበ መስቀለኛ ጥያቄ የቤቱን ጉድ
አደባባይ አወጡት። አማርኛ .... እንደሚባለው በሰለጠኑት ስል በሰየጠኑት እንደማለት አ
ድርጋችሁ እንዳትወስዱብኝ ብቻ! ኢንጅነርማ ለነገሩ ምን ያድርጉ።

እኔውም እብድ ነኝ ከወፍ የገበየሁ፣
መቀመጧን እንጅ መብረሯን የት አየሁ።

እንዳለው የወፍ ገበያተኛ ሆነው። በሌላም አነጋገር፡-

ዱሮ ነበር እንጅ መጥኖ መደቆስ፣
አሁን ምን ያደርጋል ወጭት ጥዶ ማልቀስ።

እንደሚባለው መሆኑ ነው። የቅንጅት ነገር ያሳዝናል!! እስኪ አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ል
ጠይቃችሁ? ቅንጅት በይፋ ከተቋቋመ በሁዋላ በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ በድጋፍ ድርጅ
ቶች ውስጥ ምልመላና ማሰባሰብ ሲካሄድ የቆየው በድጋፍ ድርጅቶች አመራር ውስጥ ድ
ንገት በተዘነቁ የቀስተ ደመና አባላት ነው የሚባለውን ታውቃላችሁ፣ አታውቁም? አሽሟ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጣጮቱን እንዴት ብትሏቸው አዲስ አበባ የቅንጅት አባላት ሆነው ተመርጠው በአመራር
የነበሩ ከቀስተደመና የመጡ እነአቶ ብርሃነ መዋና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን የመሳሰሉ፣ በ
ቅንጅት ስም የትም ቦታ መድረኩን እየያዙና እያቀነቀኑ፣ ቀደም ብለው የድጋፍ ኮሚቴዎ
ችን ሲያስተባብሩ የነበሩትንና ደጋፊዎችን በማግለል፣ በቅንጅት ስም ቀስተደመናዊ ቅንጅ
ትን ሲያጠናክሩ እንደቆዩ አታውቁም ወይ? ይሏችኋል። እነአንዳርጋቸውን ብትጠይቁ ደ
ግሞ ከ«ፋራዎቹ» ወገን ከሆናችሁ አይኔን ግንባር ያድርገው፤ የሰለጠነ ፖለቲካ ከሚያራም
ዱት የ«አራዳ» ጥቂት ልጆች ውስጥ ከሆናችሁ ደግሞ «ዱሮስ ከሞኝ ደጃፍ ... » ይሏች
ኋል።

አሽሟጦጮቹ የሚሉት የሚመስል ነገር ነው። ምነው ቢሉ አብዛኞቹን ወጣቶች በየፓልቶ
ኩ ሳይቀር ኮልኩለው አሁን ለተፈጠረው ልዩነት ለተራ ስድብ እንዳዘጋጇቸው ማን ያስተ
ባብሳል?

እንግዶቹም በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ በየዞሩባቸው ቦታዎች ሁሉ በተለየ መልኩ ተኮልኩ
ለው ሲጨፍሩና ሲያጨበጭቡ የሰነበቱት እነዚሁ በቀስተደመና ቅንጅታዊነት የተመለመሉ
ት እንደሆኑ የሚያውቁ ያውቋቸዋል እያሉ ይከራከራሉ። የተባሉት ሰዎች መድረኩን በያ
ሉበትም ሆነ በቅንጅት ኢንተርናሽናል አማካይነት ይዘውት ስለነበር ይኸ አልተደረገም ለ
ማለት ያዳግታል። ለነገሩማ ቅንጅት ኢንተርናሽናል ሲቋቋም ከተጻፉት ደብዳቤዎች በአን
ዱ በተለይ በእነዶክተር ብርሃኑ ግፊት መሪነቱን አንዳርጋቸው ይያዘው ብለው ለምን ጻፉ?
የጤና ነበርን?

ቀስተደመናዊ ቅንጅት በቡድን ተመካክረው፣ ሌሎቹንም ተንኮሉ ያልገባቸውን ግለሰቦች ገ
ፋፍተው፣ ኢንጅነር ሃይሉን ትተው ለመጓዝ የቸኮሉበት ምክንያት ከዚሁ ጋር የተያያዘ መ
ሆኑን በማስረጃ የሚናገሩ አሉ። ነገሩ ለማስታረቅ ሳይሆን ኢንጅነሩ ያቋቋሙትን ካውንስ
ል ለማፍረስ ነው። ምክንያቱም ከቀስተደመናዊ ቅንጅት ንክኪ የሌላቸው ሰዎች ስለተመረ
ጡ ሲሰራ የቆየው እንዳይጋለጥባቸው እየተባለ ይሽሟጠጣል።

ዶክተር ብርሃኑ እኮ ከቡድኑ በፊት ቀድመው ለንደን አንዳርጋቸው፣ አሽሟጦጮቹ እንደ
ሚጠሩት ደግሞ በትናቸውን በግል፣ አሜሪካም እነብርሃነ መዋን በተናጠል ሲያወያዩ የሰነበ
ቱት ስለቀስተደመናዊ ቅንጅት አደረጃጀት ለማወቅ ነበር የሚሉ ውስጥ አዋቂዎች አሉ።
በጉብኝቱም ወቅት የቀስተደመናዊ ቅንጅትን አሰላለፍ ካዩ በሁዋላ ሳያፍሩ፣ ከአሁን በሁዋ
ላ የሚመርጡት በየፊናው መስራትንና በገሃድ በየግል መመልመልን እንደሆነ ተናግረዋል።

ይኸም አሽሟጣጮ የሚያሽሟጥጠው ሳይሆን «ከጊዜያዊ ጉዳዮች የውይይት መድረክ»
ቀድቶ ሪፖርተር የሚባለው አዲስ አበባ የሚታተም የወያኔ ጋዜጣ ባለፈው ሳምንት በታህሳ
ስወር ባወጣው እትሙ ዶክተር ብርሃኑ በራሳቸው አፍ የተናገሩትን እንዲህ ሲል መዝግቧ
ል፦

«... እነዚህን ሃይሎች እንደገና በእርቅ አምጥቶ አንድ ቅንጅት ብሎ ለመሄድ ተፈላጊም
አይመስለኝም። ምን እንደሚጠቅም አላውቅም። ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ አንድ እርምጃ
የሚያስኬድ አይመስለኝም። ሁሉም በየፊናው ይሂድ። ሁላችሁም መንገዳችሁን ሂዱ።
ብልግናውን ተው። ለምታምኑበት እየመለመላችሁ ቀጥሉ። ... » «ቅንጅት» ለሚለው ስ
ም ደጋፊዎች እንዳይጨነቁና በእምነቱ ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው የገለጹት ዶክተር ብር
ሃኑ፣ የወደፊቱን የድርጅታቸውን ስያሜ ሀገር ቤት ያሉት ጓደኞቻቸው እንደሚያስቡበት ግ
ምታቸውን ሰጥተዋል» በማለት።

ታዲያ ቅንጅትን የፈጠርነው ላለፉት 17 አመታት የተካሄደው የተበታተነ ትግል ለህዝባዊ
ድል ሊያበቃን አልቻለም ብለን ነው በማለት ዶክተር ብርሃኑ አልተናገሩም እንዴ? ለነገሩ
ብለውስ ቢሆን በአራዳ የሰለጠነ ፖለቲካ ይህንን ማለት አያስጠይቅም፣ ከ«ፋራ ፖለቲካ»
አራማጆች ክስ በስተቀር። እናም እንግዲህ «ከራስ በላይ ንፋስ» እንደሚለው የአራዳ ል



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጆች አባባል፣ የዶክተር ብርሃኑ ዋና አላማ ቀስተደመናዊ ቅንጅትን ለማደራጀት እንደነበር አያጠራጥርም ይላሉ አሽሟጣጮች። የእስካሁኑ ጉዟቸው፦

ቢያዩኝ እሰቃለሁ፣
ካላዩኝ እሰርቃለሁ።

ነበር። አሁን ግን በየፊናችሁ ሂዱ፣ የምታምኑባቸውን ምልመላ ቀጥሉ፣ ቅንጅት ለሚለው ስም አትጨነቁ ብለው መመሪያ ሰጥተዋል። በየድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ያሉ የአመራር አባላትም በአዲስ ምርጫ እንዲዋቀሩ አመራር ሰጥተዋል ይባላል። የመጀመሪያው ቀስተደመናዊ ቅንጅት ኮሚቴ በሲያትል እንደተመረጠ ታውቋል። ሌላውም ይቀጥላል እየተባለ ይሽሟጠጣል። እንዴት ቢሉ መልሱ፦

መገን የአራዳ ልጅ፣ እነድንጋይ ኳሱ፣
ምንጊዜ ተጠርተው ምንጊዜ ደረሱ።

ነውና በሰለጠነ ፖለቲካ።

ታዲያ ኢንጅነር ሃይሉ እንዳለፈው ሁሉ በለዘብተኛነት ይኸን እያዩ ዝም ማለት አለባቸው ትላላችሁን? ለመሆኑ ላዕላይ ምክር ቤቱስ ምን እያደረገ ይሆን? የብዙዎች ጭንቅ ይኸው ነው።

አሽሟጣጭ አትጥሉ። እብድና አሽሟጣጭ ውነትን ይናገራሉ። ሌላ ቀን እንገናኝ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com